# ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)

**Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)**

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshwegenie.org

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ነሃሴ ፲፮፣ ፪ሺ ፲፭ ዓ.ም. (August 22, 2023) ቅጽ ፲ ቁጥር ፫*


## የዐማራ ህዝብ የህልውና እና የነፃነት ትግል አካል የሆነውን የፋኖን እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ድጋፍ ሊያደርግለት ይገባል!

ዐማራ ላለፉት 32 አመታት ከፍተኛ በደል እንደደረሰበት የአደባባይ ሐቅ ነው። የኦሮሙማምው አገዛዝ ዳግማዊ ኢህአዴግ/ብልፅግና ስልጣን ሲይዝ የዐማራ ህዝብ የጠቅላይ ሚንስትሩን ንግግር በመስማት ብቻ በከፍተኛ ደስታና ተስፋ ተቀብሎት እንደነበር የሚታወቅ ነው። ነገር ግን እምነት የተጣለበት የኦሮሙማው አገዛዝ/ብልፅግና የሚያራምደው ስልት የማታለልና የማደናገር ስለሆነ፣ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ቀን ጀምሮ የዐማራ ህዝብ በግፍ በጅምላ እንደበግ ታረደ፤ ግድያው የዐማራን ህዝብ ዘር ማፅዳት ስለሆነ ህጻናት፣ ነፍሰጡር፣ አዛውንትና ሽማግሌ አይመርጥም። ሁሉም በአሰቃቂ ሁኔታ ታርደው፣ በእሳት ተቃጥለውና እንደ እባብ ተቀጥቅጠው ተገደሉ። ቤተእምነቶቹ፣ በተለይም መስጊድና ቤተ ክርስቲያናት በእሳት ጋዩ። የየቤተዕምነቱ አገልጋዮች ሼሆች፣ መነኮሳትና ቀሳውስትም ከመታረድ አልተረፉም። የዐማራ ትዕግስት በጅምላ በግሬደር ከመቀበር ከቶ አላዳነውም።

በወለጋና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ የጀመረው መፈናቀል በአዲስ አበባም ቀጠለ። በአዲስ አበባ ህፃናት መጠጊያ አጥተው በጅብ ተበሉ።ዐማራ ወደአዲስ አበባ እንዳይገባ በተደጋጋሚ ተከለከለ። ዐማራ አዲስ አበባ ለመግባት ሚልዮን ብር መክፈል ግድ ሆነበት። የዐማራ ጉዳይ ያገባናል ብለው እውነት የተናገሩ ማህበራዊ አንቂዎችና ጋዜጠኞች እየታፈኑ ታስረው በአንድ ክስ በተደጋጋሚ በርከት ያለ ሺ ብር እየከፈሉ እንዲራቆቱና በህግ ተስፋ ቆርጠው ዝም እንዲሉ ብዙ ተሰራ። ዐማራ መግቢያ መውጫ እስኪያጣ ድረስ ሲዋከብ መታገሱ መከራውን አባባሰበት። በዚህም ዐማራ ትዕግስተኛ ሳይሆን ፈሪ ነው ብለው የትግሬና የኦሮሞ ነፃ አውጪዎች ተሳለቁበት። አንዳንድ በሀሰተኛው የአንድነት ትግል የደነዘዙና ራስ ወዳድ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ኢትዮጵያዊ ነን ብለው መደበቃቸው ደግሞ ለኦሮሙማው አገዛዝ ጭካኔ አስተዋፆ አደረገ።

አሁን ዐማራ ራሱን ነፃ ለማውጣት የህልውና ትግል ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረውምና የአማራ ህዝባዊ ኃይል የሆነው ፋኖ ***ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነፃነት*** ብሎ መራራውን ሕዝባዊ ትግል ሲጀምር የዐማራ ህዝብ አለኝታ በማግኘቱ እልል ብሎ ተቀበለው። ከጅምሩ በዐማራ ህዝብ ተቀባይነት ያገኘው ፋኖ በአጭር ጊዜ በርካታ ድሎችን መቀዳጀቱ ለህዝቡ ከፍተኛ የሞራል ስንቅ ሆነው። በዚህ አጋጣሚ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅትም የህልውና ትግሉን ሙሉ በሙሉ እንደሚደግፍና ለፋኖ ትልቅ ክብር እንዳለው ይገልፃል።

የዐማራ ህዝብን ወክያለሁ የሚለውና ዐማራን ከ 32 ዓመታት በላይ ለዚህ መከራ የዳረገው ብአዴን/አዴፓ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ይልቃል ከፋለ ቀደም ሲል የክልሉ ምክር ቤትን ሳይሰበሰብና ምክር ቤቱ ሳይወስን ለቀደሙት ሶስት ወራት ወታደራዊ ስርዓት ክልሉን እንዲመራ ማድረጋቸው ሳያንስ፤ አሁን ደግሞ ይባስ ብለው ፀረ ዐማራ የሆነውን የአገዛዙን ህግ እንኳን ሳይጠብቁ፤ የክልሉ ምክር ቤት ተሰብስቦ ሳይወስንና ሳያፀድቅ፤ በግላቸው ከህግ ውጭ የአማራ ህዝብ በፌዴራል ኃይል በጉልበትና በወታደራዊ አገዛዝ እንዲገዛ፣ እንዲጨፈጨፍና የቀረውም ባሪያ እንዲሆን ጥሪ አቀረቡ። ይህም የኦሮሚማው አገዛዝ አማራውን ትጥቅ አስፈትቶ በማንበርከክ በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ የኦሮሚማ ሀገርን ለመፍጠር የያዘውን ግብ የማስፈጸም አካል መሆኑ ግልጽ ነው።

በዚህም መሰረት፣

- የብልፅግና መሩ የኦሮሙማ አገዛዝ በክልሉ በኦሮሞ ክልል ያሉትን ባንኮች ሁሉ የሚዘርፈውንና ንፁሀንን አጋድሞ እንደበግ የሚያርደውን የኦሮሙማ ክንፍ "ሸኔ"ን በእንክብካቤ ይዞ፤ የሀገር ጠበቃ በተለይም የዐማራ ህዝብ ብቸኛ ዋስትና የሆነውን ፋኖን በሀገሩና በወገኑ ላይ አንዳችም ወንጀል ሳይሰራና ሳይዘርፍ እንደዘራፊና ወንበዴ እንዲቆጠር መንግሥታዊ የስም ማጥፋት ዘመቻ ተፈፅሞበታል።
- የመከላከያ ኃይሉ የአገሩን ዳር ድንበር ማስጠበቅና ሰላም ማስፈን ሲገባው፣ ወታደሩ አላስፈላጊ መስዋእትነት እንዲከፍል አደረገ። መከላከያው በድሮንና በጦር አውሮፕላን በመታገዝ በዐማራ ህዝብ ላይ ጭፍጨፋና ነፃ እርምጃ በመፈፀም የዘር ማጥፋቱን አጠናክሮ ቀጠለ። በዚህም መከላከያው አገራዊ ትልዕኮውን ወደ ጎን ትቶ የኦሮሚማ/ብልጽግና የግል ወራሪ ሰራዊት በመሆኑ ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት እየሰራ ይገኛል።
- በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎችም ክልሎች ጭምር የዐማራ ተወላጆች ማንነታቸው እንደወንጀል ተቆጥሮ ከ15 እስከ 20 ሺህዎች የሚቆጠሩ ንፁሀን በመንግሥታዊ አፋኝ ቡድን ታፍነው በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች ሳይቀር ያለፍርድ

እንዲታጎሩ ተደርጓል። ቁጥራቸውም በውል የማይታወቁ የዐማራ ተወላጆች የደረሱበት ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው በጭንቅ ላይ ይገኛሉ።

- የኦሮሙማው አገዛዝ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተገን አድርጎ በየቦታው ያጎራቸው የዐማራ እስረኞች በከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ዛቻ፣ ማስፈራሪያና ግድያ እየተፈጸመባቸው ነው።

ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት ከአለፈው የትግል ልምዱ በመነሳት የኦሮሙማውን አገዛዝ ከላይ የተዘረዘሩትን አታድርግ ማለት፣ "አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አቤት አይልም" እንዲሉ ጉንጭ ማልፋት እንደሆነ ያምናል። ስለዚህ የዐማራ ህዝባዊ ኃይል ፋኖ በዐማራ ህዝብ ቅቡልነት ያገኘ ብቸኛው የዐማራ አለኝታና ተስፋ ስለሆነ ትግሉን አጠናክሮ በመቀጠል ከዳር ማድረስ ይኖርበታል። ለዚህም ዐማራውን ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረገው ሥርዓቱ ስለሆነ ነፃነቱን የሚያገኘው ታግሎ ባመጣው ድል የሚፈልገውን ስርዓት ማስፈን ሲችል ብቻ ነው።

ነገር ግን አሁንም ዐማራን በሃሰት የኢትዮጵያዊነት ካባ ተሸብበው ሲያስጠቁ የኖሩ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች የስርዓቱ ተቃዋሚ መስለውና የዐማራ ተቆርቋሪ ሆነው ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። ስለዚህ እያንዳንዱ ዐማራም ሆነ ፋኖ የዐማራውን የህልውና ትግል በመጥለፍ ወኪል ለመሆን ከሚያንዣብቡት ተኩላዎች ተጠብቆ በራሱ መቆም ይኖርበታል። ***በድርድርም ሆነ በሽምግልና የሚመጡት ሁሉ ገዥውን ስርዓት ለማስቀጠል እንደሆነ በኦርቶዶክሳውያንና በሙስሊሞች የሸንገላ የኦሮሙማ የሽምግልና ትምህርት መውሰድ ይኖርብናል። ዐማራው ከአሁን በኋላ መወከል ያለበት መስዋእትነት በሚከፍሉ እና የአማራውን ትግል በማይክዱ ልጆቹ ብቻ መሆን ይኖርበታል።***

ድርጅታችን ቀደም ሲል በኢህአዴግ ለ27 ዓመት፣ በመቀጠልም በየኦሮሙማምው አገዛዝ ዳግማዊ ኢህአዴግ/ብልፅግና ለ5 ዓመት፣ ብሔር ብሔረሰብ በሚል ሸንገላ የተበታተነው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ዐማራ ከተዳከመ በኋላ በኦሮሙማ እንደሚጨፈለቅና በዐማራ ላይ የተቃጣው ሁሉ የሁሉም የኢትዮጵያ ነገዶችና ማህበረሰቦች እጣ ፈንታ እንደሚሆን በመገንዘብ ለዐማራ ሕዝባዊ ኃይል ፋኖ የህልውናና የነፃነትን ትግል ሙሉ ድጋፍ እንዲያደርግና አገሩን ኢትዮጵያን እንዲያስቀጥል ማሳሰብ ይወዳል።

ዐማራውም "አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ! ሁሉም ዐማራ ለአንድ ዐማራ!" በሚል አላማ ተናቦ ከቆመና ለፋኖ ድጋፍ ካደረገ የመከራው ቀን ያጥራልና ለዚህ በውጪም ሆነ በአገር ውስጥም ያለ ሁሉ አስተዋፅኦ ማድረግ ይኖርበታል። በህዝባዊ እንቢተኝነት ውጤታማ መሆኑን በተግባር ያስመሰከረው የዐማራ ህዝባዊ ኃይል ፋኖ ለድል እንደሚበቃና ዐማራ እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ሰብአዊ መብቱ ተጠብቆ እንደሚኖር ሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት አይጠራጠርም።

የዐማራ ሰባዊ መብት ይከበር!

የብልጽግና እና ተባባሪ አንባገነኖች የመብት ጥሰት፣ ግድያ፣ ማሰቃየት፣ ዛሬውኑ ይቁም!